በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

ሰ/መ/ቁ፡-202737

ቀን፡-29/03/2014ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ አቶ ረጋሳ ጉርሙ ጠበቃ ጋዲሳ ቡታ ቀረቡ

ተጠሪ፡ ወ/ሮ ዘነበች ግ/መንፈስ- ጠበቆች ዘበነ ፍቅሬ እና አዲሱ አየነው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ያለፍርድ ቤት ፈቃድ በተወዉ ጉዳይ ላይ የቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም ተብሎ የተሰጠዉን ብይን ለማስለወጥ ነዉ፡፡የክርክሩ መነሻ የቤት ሽያጭ ውል የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ላይ የአሁኑ አመልካች ከሳሽ በመሆን የአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ከሚች ባለቤታቸው አቶ ተሾመ አፈወርቅ ጋር በመሆን በቀን 06/12/1996 ዓ.ም በአ/አ/ክ/ቂ/ክ/ክተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 047 የካርታ ቁጥር ሴ.ኬ.አሲ/02/31/1229/001040/01 የሚታወቅ መኖሪያ ቤት ለአመልካችና ለአቶ ፀጋዬ ግ/መንፈስ ሽጠዋል፣ቤቱን እንዲለቁ ሲጠየቁ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/153563 ቤትን አንዲለቁልኝ ክስ አቅርቤ ፍ/ቤቱን አስፈቅጄ ያነሳሁት ቢሆንም ተጠሪ ቤቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ተጠሪ ቤቱን ለቀው እንዲወጡና እንዲያስረክቡኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋዋል፡፡ተጠሪ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በበኩላቸዉ በቀን 12/05/2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረበውት መልስ አመልካች በመ/ቁ.153563 ላይ ቤቱን ከተጠሪ ለመረከብ ተመሳሳይ ክስ አቅርቦ አመልካቹ በውሉ በተመለከተው ጊዜ የሽያጭ ገንዘቡን ባለመክፈሉ የውል ግዴታውን ስላልተወጣ የባለቤትነት መብት ስለሌው ለቀን ልናስረክብ እንደማይገባ መከራከሪያ አቅርበን እያለ አመልካች በቀን 10/04/2011ዓ.ም በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.278 መሰረት በፈቃዱ ክሱን ለመተው ማመልከቻ አቅርቦ ፍ/ቤቱም በ11/04/2011ዓ/ም ከሻስ ክስ በማቋረጡ ለተጠሪ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍል በማለት መዝገቡን ዘግቷል፣ስለሆነም ያለፍርድ ቤት ፈቃድ በተወዉ ጉዳይ አዲስ ክስ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም፣በተጨማሪም የቤት ሽያጭ ውሉ ተፈጽሟል የተባለዉ ከ16 እና ከ17 ዓመታት በፊት ስለሆነ በፍ/ህ/ቁ/1845 መሰረት በ10 ዓመት ይርጋ ይታገዳል፣እንዲሁም በፍ/ህ/ቁ. 2892(3) መሰረት ሻጩ ውሉን እንደ ውሉ ቃል ከመፈፀም መዘግየቱን ከተረዳበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1(አንድ) ዓመት ድረስ ውሉ እንዲፈፀምለት ካልጠየቀ በቀር ገዢው ውሉ በግዴታ እንዲፈፀም የማድረግ መብቱን ያጣል፣ስለዚህ በ1 (አንድ) ዓመት ውስጥ ስላልጠየቀ በይርጋ ውድቅ ይደረጋል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በፍሬነገር ረገድ አማራጭ ክርክር ማቅረባቸዉን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ፍ/ቤቱም በተጠሪ በኩል የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የግራ ቀኝ ክርክር ሰምቶና መርምሮ በመጀመሪያዉ ክስ አመልካች ክሱ እንዲቋረጥ አቤቱታቸውን ሲያቀርቡ ሌላ ጊዜ ክስ ለማቅረብ ፍርድ ቤቱ እንዲፈቀድላቸው የጠየቁ ሳይሆን ክርክሩ እየገፋ በመምጣቱ ውጣ ውረዶች ስለበዛባቸው ክሱን ማቋረጥ እንደፈለጉ የሚያሳይ ነው፡፡ፍ/ቤቱም ከሳሽ(የአሁኑ አመልካች) ያቀረቡትን አቤቱታ በመቀበል ከሳሽ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 278 /2/ መሰረት በማየት ጉዳዩን በተመለከተ አዲስ ክስ እንዲያቀርቡ አልፈቀደም፡፡እንዲህ ከሆነ አመልካች ክሱን የተውት ከፍ/ቤት ፈቃድ ውጭ እንደሆነና አመልካች አስፈላጊውን ኪሳራ ለተጠሪ ከፍለው መዝገቡ መዘጋቱን እንዲሁም አመልካችም ጉዳዩን በተመለከተ አዲስ ክስ ማቅረብ እንደማይችል በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.279(1) ስር ተደንግጓል፣ስለዚህ አመልካች አሁን አዲስ ክስ ማቅረባቸው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 278(2) እና 279(1) መሰረት አግባብነት የለውም በማለት ክሱን ውደቅ አድርጓል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ይግባኙ አያስቀርብም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰት መዝገቡን ዘግቷል፡፡የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፣ቤቱን እንዲለቁልኝ ሲጠይቅ ተጠሪ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.153563 ላይ ክስ መስርቼ ስንከራከር ከቆየን በኋላ ፍ/ቤቱን አስፈቅጄ ክስ ያቋረጥኩበት ምክንያት ተጠሪ የባለቤቱ እህት በመሆናቸው እና ተጠሪ የሽያጭ ውል ይፍረስልኝ ጥያቄም ውሉ ህጋዊ ነው ተብሎ ስለተወሰነ ከዚህ በኋላ ተጠሪ አለቅም የሚሉበት ምንም ህጋዊ ምክንያት የለም በፈለኩ ጊዜ ይለቁልኛል በሚል እሳቤ ፍ/ቤት አስፈቅጄ ክሱ ተቋርጧል፡፡ ፍ/ቤት ሳላስፈቅድ በራሴ ፈቃድ ለመተው ቢፈልግ ኖሮ ፈቃድ ለመጠየቅ አቤቱታ ለፍ/ቤት ባላቀረብኩ ነበር፡፡የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 279(1) የሚመለከተው በራሱ ፈቃድ

ፍ/ቤትን ሳያስፈቅድ ክሱን የተወ ወይም ያቋረጠ ከሳሽን ሲሆን እኔ ግን ለፍ/ቤት አመልክቼ ፍ/ቤቱም ክሴን እንዲተው የፈቀደልኝ መሆኑን የቀረበው ማስረጃ ያረጋግጣል፡፡ስለዚህ አዲስ ክስ ማቅረብ አትችልም በማለት የተሰጠው ብይን የንብረት ባለቤት የመሆን መብቴን የሚቃረን ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ብይን ነው በማለት ብይኑ እንዲታረም አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ለክርክር ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ግራ ቀኙ ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም በሚል የተሰጠ ውሳኔ ጸንቶ ባለበት ሁኔታ ተጠሪ ቤቱን እንዲለቁ አመልካች በስር ፍ/ቤት ተጠሪ ላይ ያቀረቡትን የክስ አቤቱታ ቀደም ሲል ተጠሪ ቤቱን ይልቀቁልኝ ብለው ክስ አቅርበው በራስዎ ፈቃድ አመለክተው እንዲቋረጥ አድርጓል በማለት አቤቱታቸው ውድቅ የተደረገበትን አግባብነት ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ 278 እና 279 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸዉ በቀን 30/11/2013ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት መልስ በስር ፍርድ ቤት እየተከራከርን እያለ አመልካች ክሱን መተዋቸውን ለፍ/ቤት አመልክተዋል፣ነገር ግን ወደ ፊት በሙሉ ወይም በከፊል አዲስ ክስ የማቅረብ መብት አልጠየቁም፣አላስጠበቁም፣የጀመርኩት ክስ በሙሉ ፍቃድ ማቋረጠን አረጋግጣለሁ የሚል እንጂ አዲስ ክስ ለማቅረብ አይደለም፣የፍ/ቤቱም ትእዛዝ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 278(1) መሰረት ክስ መቋረጡ ያረጋግጣል፡፡በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 278(1) መሰረት ክስ ሲቋረጥ ወደፊት ክስ ለማቅረብ ያልተፈቀደለት መሆኑን በፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.116869 እና 158314 ላይ አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቷል፣አዲስ ክስ ማቅረብ የሚቻለው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 278(2) መሰረት በፍ/ቤት ፈቃድ ሲቋረጥ ነው፡፡ይርጋን በተመለከተ አመልካች ያቀረበው የመፋለም ክስ ሳይሆን በሽያጭ ውል መነሻ ተገደው ቤቱን እንዲያስረክቡኝ የሚል ስለሆነ እና በስር ፍ/ቤት ያልተነሳና በዚህ ረገድም የህግ ስህተት እንዳልተፈፀመ ስለተረጋገጠ አቤቱታው ውድቅ ሆኖ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡ መርምረን እንደተገነዘብነዉ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ተጠሪ የሸጡላቸዉን ቤት ለቀዉ እንዲያስረክቧቸዉ እንዲወሰን የሚል ሲሆን ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ የዳኝነት ጥያቄ በመ/ቁ.153563 ላይ አቅርበዉ አመልካቹ ክሱን ለመተዉ ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት መዝገቡ የተዘጋ መሆኑ አላከራከረም፡፡ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካች ክሱን ሲያቋርጡ አዲስ ክስ እንዲያቀርቡ ፍርድ ቤቱ አልፈቀደላቸዉም በማለት ነዉ፡፡አመልካች አጥብቀዉ የምከራከሩት ክሱን ያቋረጥኩት ፍርድ ቤቱን አስፈቅጄ ስለሆነ አዲስ ክስ ከማቅረብ አያግደኝም በማለት ነዉ፡፡

በህግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር የፍትሓብሔር ክርክር የሚመራዉ በፍትሓብሔር ስነስርዓት ህግ በተደነገገዉ አግባብ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 1 ድንጋጌ ይዘት የምንገዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡የፍትሓብሔር ስነስርዓት ህግ ዓይነተኛ አላማ የፍትሓብሔር ክርክር የሚመራበትን ስርዓት በመደንገግ የፍርድ ሂደት በፍትሃዊነት እንዲመራ በማድረግ የተከራከሪ ወገኖችንም ሆነ የፍርድ ቤቱን ሀብት እና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ ክርክሩ እልባት እንዲያገኝ ማስቻል ነዉ፡፡ይህንኑ ዓላማ ለማስካት ያስችላሉ ተብለዉ ከተዘረጉት ስርዓቶች አንዱ ከሳሽ ወገን በአንድ ጉዳይ ላይ ተደጋጋሚ ክስ እንዳያቀርብ ለመከላከል የተዘረጋዉ ስርዓት የሚመለከት ነዉ፡፡በዚህ መዝገብ ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት ያለዉ ከሳሽ ወገን ክሱን ለመተዉ መቻሉና ዉጤቱን የሚመለከተዉ ድንጋጌ ነዉ፡፡

አንድ ክስ ከቀረበ በኋላ በማናቸዉም ጊዜ ከሳሹ ያቀረበዉን ክስ በማንሳት ከተከሳሾቹ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ከክሱ ዉጭ ለማድረግ ወይም ያቀረበዉን ክስ በሙሉ ወይም በከፊል ለመተዉ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 278/1/ ስር የተመለከተ ሲሆን ፍርድ ቤቱ አቤቱታዉን ተቀብሎ ትእዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ከሳሽ ወገን ክሱን ለማንሳት ወይም ለማቋረጥ የጠየቀበትን ምክንያት መርምሮ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ከሳሹ አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚችልበትን መብት መጠበቅ የሚችል ስለመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ (2) ስር ተመልክቷል፡፡ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ በአንድ በኩል ከሳሹ በግል ጉዳዩ ላይ የመወሰን መብቱን ተጠቅሞ ክሱን ለመተዉ የሚችል መሆኑን በሌላ በኩል ከሳሹ በፈቃዱ በተወዉ ነገር ላይ አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚችለዉ ፍርድ ቤት መብቱን የተጠበቀለት ሲሆን ብቻ መሆኑን ነዉ፡፡በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 278/2/ ስር እንደተመለተዉ ከሳሹ በሌላ ጊዜ አዲስ ክስ እንዲያቀርብ ሊፈቅድለት የሚችለዉም በክሱ አቀራረብ ስርዓት ጉድለት ያለበት ሲሆን ወይም አዲስ ክስ ለማቅረብ ሊያስፈቅድለት የሚችል በቂ ምክንያት ሲኖር እና ፍርድ ቤቱ ምክንያቱን ተቀብሎ መብቱን የጠበቀለት እንደሆነ ነዉ፡፡በሌላ አገላለጽ በቁጥር 278/2/ የተነገረዉን ባለመጠበቅ ከሳሹ ከፍርድ ቤት ፈቃድ ሳይቀበል ክሱን በሙሉ ወይም በከፊል የተወ እንደሆነ አዲስ ክስ ለማቅረብ እንደማይችል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 289/1/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ስለዚህም የቀረበዉ አዲስ ክስ ተገቢነት ያለዉ መሆን አለመሆኑ የሚወሰነዉ ክሱ በፍርድ ቤት ፈቃድ ወይም ያለፍርድ ቤት ፈቃድ የተቋረጠ ወይም የተተወ መሆን አለመሆኑ በመመርመር እንደሆነ ያስገነዝበናል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይዘት መገንዘብ እንደተቻለዉ አመልካች ቀደም ሲል በዚሁ ጉዳይ በመ/ቁ/ 153563 ላይ ያቀረበዉን ክስ ለመተዉ መፈለጉን ገልጾ ለፍርድ ቤቱ ባቀረበዉ ማመልከቻ መሰረት መዝገቡ የተዘጋ ስለመሆኑና መዝገቡም የተዘጋዉ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ 278/1/ መሰረት መሆኑን ያመላክታል፡፡የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ መርምሮ አመልካች ክሱን የተወዉ ሌላ ጊዜ አዲስ ክስ ለማቅረብ ከፍርድ ቤቱ ፈቃድ አግኝቶ አለመሆኑንና ያቀረበዉም ማመልካቻ ፈቃድ ለመጠየቅ ሳይሆን ክሱን መቋረጡን ፍርድ ቤቱ እንዲያዉቀዉ ለማድረግ የቀረበ ስለመሆኑ ይዘቱን ቁምር በመመርመር ያረጋገጠዉ ጉዳይ ነዉ፡፡አመልካች አሁንም የሚከራከረዉ ለፍርድ ቤቱ ያቀረበዉ ማመልካቻ ፍርድ ቤቱን ለማሳወቅ ተደርጎ መወሰዱ ስህተት ነዉ የሚል ነዉ፡፡ይሁንና መዝገቡ እንደሚሳየን አመልካች በቀን 10/04/2011ዓ.ም ለፍርድ ቤቱ ያቀረበዉ ማመልከቻ ይዘት ‹‹...ክርክሩ

እየገፋ በመምጣቱ ከሳሽ አላስፈላጊ ዉጣ ዉረዶችን በመተዉ የጀመርኩትን ክስ ክርክር በሙሉ ፈቃድ ክሴን ለማቋረጥ ...›› በሚል በቃለ መጎላ ተደግፎ የቀረበ አቤቱታ መሆኑን የሚገልጽ እንጂ በጉዳዩ ላይ ሌላ ጊዜ አዲስ ክስ ለማቀርብ የፍርድ ቤቱን ፈቃድ የጠየቀ መሆኑን የሚያሣይ አይደለም፡፡ክሱን ለማቋረጥ ያቀረበዉም ምክንያትም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 278/2/ ስር ከተደነገጉት ምክንያቶች አንዱም ስለመኖሩ የማያሳይ ነዉ፡፡ፍርድ ቤቱ ማመልከቻዉን መርምሮ የሰጠዉ ትእዛዝ ይዘትም ክሱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 278/1 መቋረጡን የሚገልጽ እንጂ አዲስ ክስ ለማቅረብ መብት የተጠበቀለት መሆኑን አያሣይም፡፡የመዝገቡ ይዘት ይህንን የሚያሳይ ሆኖ እያለ አመልካች ፍርድ ቤት ፈቃድ አግኝቻለዉ በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ መሰረት ያለዉ ሆኖ አላገኘም፡፡ከዚህ አኳያ በተጠሪ በኩል የቀረበዉን መቃወሚያ መነሻ በማድረግ የስር ፍርድ ቤትም መ/ቁ/153563 ላይ የተጀመረዉ ክርክሩ የተቋረጠበትን አግባብ መርምሮ ከሳሹ ክሱን በራሱ ፈቃድ የተወዉ መሆኑን እንጂ በፍርድ ቤት ፈቃድ የተወዉ መሆኑን የሚያሣይ አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ ስህተት ነዉ የሚባልበት ምክንያት የለም፡፡እንዲህ በሆነ ጊዜ ደግሞ ከሳሽ ወገን በዚያዉ ጉዳይ ላይ አዲስ ክስ ማቅረብ እንደማይችል የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 289/1 በግልጽ ደንግጓል፡፡የስር ፍርድ ብይን መሰረቱም ይኸዉ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሰል ክርክሮች ላይ ይህ በሰር ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔም ይህንኑ የሚያጠናክር ነዉ፡፡ሰበር መ/ቁ/116869 ፣158314 እና ሌሎች መመልከት ይቻላል፡፡

ሲጠቃለል በዚህ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ ይህንኑ የሥነስርዓት ህግ ድንጋጌ እና በተመሳሳይ ክርክሮች ላይ ሰበር ችሎቱ የሰጠዉን ዉሳኔ ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አልተገኘም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

ዉሳኔ

1ኛ/የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/236492 ላይ በቀን 29/09/2012ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና ይህንኑ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/194704 ላይ በቀን 30/04/2013ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ጽንቷል፡፡ 2ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማነታወሸ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም